# ዴሞክራሲያ

* የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ልሳን *

**ዴሞክራሲያ ቅጽ 39 ቁ. 2** **ጥቅምት 2006 ዓ.ም**

## የፖለቲካ ነፃነት፣ የእኩልነት መብትና
## የሃይማኖት ጥያቄ በኢትዮጵያ

በወያኔ አገዛዝ አማካኝነት በሀገራችን የተዘረጉት የአፈና፤ የጭቆናና የመብት ጥሰቶች ከምንጊዜውም በበለጠ አይነታቸውንና መልካቸውን እየቀያየሩ ዜጎች ያለ ምክንያት የሚሰቃዩባት፤ የሚገደሉባት፤ በርካታዎች በሁለተኛ ዜግነት የሚታዩባት ሆናለች። እንዲሁም የሃይማኖት እኩልነትና ነፃነት የማይከበሩባት፤ የዜግነት መብታቸው የሚደፈጠጥባት እንደሆነች በተለያዩ ጊዜያት የተለያዩ ለሰብዓዊ መብት ተከራካሪ በሆኑ በተለይም ሀገር በቀል በሆነው የኢትዮጵያ የፖለቲካ እስረኞች አንድነት ኮሚቴ አማካኝነት እየወጡ ያሉ የይፋ መግለጫዎች በስፋትና በዝርዝር የሚገልፁት ነው። አፈናና እመቃ፣ ደብዛ ማጥፋት፣ አሰቃቂ ስየል፣ ፍጅት፣ ኢፍትሀዊ እርምጃዎች፣ ህዝብን በብሔረሰቡና በሃይማኖቱ መለያየት፤ ሀገርን ለባዕድ አሳልፎ መስጠት፤ ጫካን መጨፍጨፍና የአካባቢ ደህንነትን ማበላሸት፤ ሕዝብን ከሕግ ውጭ ማጥቃትና ለጦርነትም መማገድ፣ ...ወዘተ የተጠቀሱና የተወገዙም ናቸው።

የወያኔ አገዛዝ ራሱ የደነገገውን ሕግ ራሱ እየጣሰ በተለይም በሃይማኖት የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ እየገባ ማተራመሱና ተቋሞቻቸውን የሥርዓቱ ተቀጥያ ለማድረግ በሚያካሂደው ጥረት የተለያዩ ግፎችን በመፈፀሙ ተቃውሞ የሚያሰሙ ምዕመናን ዜጎቻችን ቁጥር እየተበራከተ መሆኑን የምንመለከተው ነው። የክርስትና እምነት ተከታዮች ባለፉት 20 አመታት የወያኔ አገዛዝ የራሱን የካድሬ ካህናት በመሪነት አያስቀምጥብን፤ በመካከላችን አይሰግስግብን፤ ገዳማት አይደፈሩ፤ ምዕመናኖቻችን አይጨፍጨፉ፤ በገዳማት የሚኖሩ መነኮሳቶቻችን መብታቸው አይደፈር፤ በባዕዳን ሰርጎ ገቦች ቤተክርስቲያኖቻችን አይዘጉብን፤ አይፍረሱብን በሚሉና በሌሎችም የምዕመናኑ ተቃውሞ ቀጥሎ ይገኛል። ሌሎችም የክርስትና እምነት ተከታዮች በተመሳሳይ ሁናቴ በአገዛዙ እየገጠማቸው ያለውን የመብት ጥሰት በመቃወም መንቀሳቀሳቸውንም የምንመለከተው ነው። የእስልምና እምነት ተከታይ የሆኑ ዜጎቻችንም በበኩላቸው ከሁለት ዓመት በፊት የጀመሩት ሰላማዊ የተቃውሞ እንቅስቃሴ ግለቱ እየጨመረ በመምጣቱ ከሌሎች የመብት ጥያቄዎች ጋር ተዳምሮ በአሁኑ ወቅት የሃይማኖት ጥያቄን በፖለቲካው መድረክ ዋና የመነጋገሪያ አጀንዳ እንዲሆን አድርጎታል። በየጊዜው እየወጡ ያሉ ሀተታዎች የሚያመለክቱትም ይህንኑ ነው። ኢሕአፓ የርዕሱን ወሳኝነት ገና ከጥንስሡ የሚኖረውን አንደምታ በመገንዘብና የተጀመረው የሕዝባዊ ትግሉም አቅጣጫ ፈሩን እንዳይስት በተለያዩ ጊዜያት በተከታታይ እይታውን ለሕዝብ ግልፅ ማድረጉ የሚታወስ ነው።

በተደጋጋሚ ለመግለፅ እንደተሞከረው የሃይማኖት እምነትን አስመልክቶ ለሚከሰቱ ችግሮች በአግባቡ መፍትሄ ካልተገኘላቸው ሂደቱን ለመቆጣጠር ወደማያስችል ሁኔታ ስለሚወስድ ሀገር ወዳዶችና ለሕዝብ ቀናዒ የሆኑ ኢትዮጵያዊ ኃይላት ሁሉ ተገቢውን ትኩረት እንዲሰጡ ኢሕአፓ አሳስቧል፤ ቀስቅሷል። ከሁሉም በላይ ደግሞ በፖለቲካውና በሃይማኖት መካከል የሚኖራቸውን ግንኙነቶች መተንተኑና ግልፅ ማድረጉ ለመፍትሄ ፍለጋው ጠቃሚነቱ የማይታበል ነው ሲልም በጥሞና ገልጿል። ፖለቲካ ሲባልም

የፖለቲካ ነፃነትና ከዚሁ ጋር ተያይዞ ያለውን የመብት ሁኔታን የሚገልፅ ነውና ይህ መብት በተወሰነ የታሪክ ወቅት ከሥልጣን በተቆናጠጡ አምባገነኖች በገደብና በችሮታ የሚሰጥ አይደለም ሊሆንም አይችልም ሲልም በስፋት አስረድቷል። የአንድ ሀገር ሕዝብ የፖለቲካ ነፃነቱ ተከብሯል ተብሎ በሚነገርበት ጊዜ የሚሰጠው ግንዛቤ በሀገሪቱ የሕግ የበላይነት ሰፍኖ በርካታው ሕዝብ የነፃነቱ ተጠቃሚ መሆን ችሏል ሲባል ብቻ መሆኑንም አፅንዖት በመስጠት በዝርዝር ግልፅ አድርጓል።

እንደ ኢትዮጵያ በመሰሉ በርካታ እምነቶች በሚመለኩበትና ሕብረተሰቡ የመድበላዊነት ጠባይ በሚያንፀባርቅበት ሁኔታ የሃይማኖት ጥያቄ በጥንቃቄና አርቆ አስተዋይነት በተሞላበት መልክ ካልተያዘ በሕዝብ አንድነት፣ በሀገራዊ ሉዓላዊነት ላይ የሚያስከትለው አደጋ በጣም ከፍተኛ በመሆኑ የዴሞክራሲ ሥርዓት ለመገንባት የሚደረገው ትግልና ሂደት ከፍተኛ እክል የሚገጥመው እንደሆነም ይኸው የ22 ዓመቱ ችግርና ሰቆቃ የሚያመላክተው ነው። ስለሆነም የሃይማኖት ጥያቄ ሁኔታው በሚጠይቀው መሠረት አንስቶ በጉዳዩ የጠራ አቋም እንዲያዝ መጣር ተገቢነቱና አስፈላጊነቱ የማይታበል መሆኑም በዚሁ ምክንያት ነው። በመሆኑም ጥያቄውን መልክ አስይዞ ለማብራራት ያመች ዘንድ፤ በቅድሚያ ስለ ፖለቲካ ነፃነትና የዜጎች እኩልነት በኢሕአፓ እይታ ውስጣዊ ይዘቱን አጠር ባለ መልኩ በመንደርደሪያነት ማቅረቡ አግባብነት ይኖረዋል።

ኢሕአፓ ከተመሰረበተ ጊዜ አንስቶ እስካሁን ድረስ በፅናት የታገለለትና አሁንም ድረስ እየታገለ፤ በርካታ መስዋዕት የከፈለበትና አሁንም ድረስ እየከፈለ የሚገኘው ለዜጎች የፖለቲካ ነፃነትና የእኩልነት መብት ያለገደብ መከበርና ሕጋዊ ዋስትናንም ማግኘት ነው። ከዚያም በላይ ብዙሀኑ ሕዝብ በፍላጎቱና ሊያደርግ በሚችለው የአካልም ሆነ የመንፈስ አስተዋፅዖ ተጠቃሚ የሚሆንበት የፖለቲካ ምህዳር እንዲመሠረት ነው። ይህንን ቅን ሃሳብ ደግሞ በርካታው ሕዝብ፤ ሀገር ወዳዶችና ለሕዝብ ቀናኢ የሆኑ ሁሉ አጥብቀው የሚስማሙበት እንደሆነ በሚያደርጓቸው እንቅስቃሴዎች ያረጋግጡት ነው።

የፖለቲካ ነፃነት አይነተኛ ጠባይ ያለው በእያንዳንዱ ግለሰብ መብት ላይ የሚመረኮዝና የሚያነጣጥር፤ በግልም ሆነ በወል በመደራጀት የራስን አመለካከትና ፍላጎት ወደ ፖለቲካው መድረክና በሀሳብ ግንባታና የውሳኔ ሂደት በማቅረብ በውይይቱ ተካፋይ ለመሆን የሚያስችል መብት ነው። ይህ የፖለቲካ ነፃነት በነፃ የመደራጀትና ከመንግሥትም ሆነ ከተለየ ቡድን ያለምንም ጣልቃ ገብነት የመንቀሳቀስን መብት የሚያጠቃልል ነው። ሰብዓዊ መብት ከሥረ መሰረቱ የግለሰብ መብት ሲሆን ሰው ሰው ሆኖ በመፈጠሩ ብቻ የተቀዳጀው ነው። ሰብዓዊ መብት የግል ነው ሲባል የሚሰጠው ግንዛቤ ይህ መብት የወል ጥገኛ እንዳልሆነ የሚያመላክት ነው። እንዲያውም የወል መብት ምንጩ ከግለሰብ መብት የሚፀነስ ነው። የእምነትና የሃሳብ ነፃነት መብትም መሠረታዊ ተብለው ከሚቆጠሩት ሰብዓዊ መብቶች ውስጥ በመሆናቸው ይህንን መብት ተግባራዊ በማድረግ የእምነቱ ተከታዮች ተጠቃሚ እንዲሆኑ መድረኩን ማመቻቸት በሥልጣን ላይ ከተቆናጠጠ ቡድን ምንጊዜም ቢሆን መጠየቅ የሚገባቸው እሴቶች ናቸው።

የፖለቲካ ነፃነት መረጋገጥ የሕሊና፤ የሃሳብ፤ የእምነትና የአስተሳሰብ ነፃነት መብት እንዲከበር መጠየቅን የሚያጠቃልል ነውና ማንኛውም ግለሰብ ዜጋ  አንድን እምነት (ርዕዮተ-ዓለምን ያካትታል) በራሱ ግላዊ ምርጫ በነፃነት ለመቀበልና ለማምለክ፤ ለራስ መገለጫ አድርጎም ለመጠቀም፤ ካልተስማማው ለመቀየር፤ በግልም ሆነ በጋራ ሲፈልግ ብቻውን በልቦናው የማመን ወይንም ከሌሎች ጋር በማህበረሰብ በአደባባይ ወይንም በፀሎት ሥርዓት ቦታ ተካፋይ በመሆን፤ በማዘውተር፤ በመማርና በማስተማር መተግበርን ሁሉ ይህ መብት የሚያጠቃልል ነው።  ማንኛውንም እምነት በሰላማዊ መንገድ ምንም አይነት የኃይልና የተፅዕኖ እርምጃ ሳይወሰድ ለማስፋፋት፤ በእምነቱ መሰረትም እሴቶቹ የሚላቸውን መንከባከብና ተግባራዊ ማድረግ፤ ነፃነቱ መጠበቅና ዋስትና ማግኘት የሚኖርበትም በዚሁ ምክንያት ነው። ለዚህም ነው አማኝ የመረጠውን እምነቱን እንዳያመልክ ሊታገድ ወይም በሥልጣን ባለ አገዛዝ አማካኝነት በሌላ እንዲተካበት ማድረግ(አህባሽን ይመለከቷል) ሰብዓዊንና ዴሞክራሲያዊ መብትን መጣስ ነውና በጥብቅ

መወገዝ ያለበት ነው ተብሎ አፅንዖት በተሞላበት ሁኔታ በተደጋጋሚ በኢሕአፓ ያለማሰለስ እየተነገረ የሚገኘው። የፌደራል ጉዳዮች ሚኒስትር የሆነው በኃምሌ 2003 ዓ.ም. በጊዮን ሆቴል በሰጠው ጋዜጣዊ መግለጫ "ይህንን (አህባሽን ማለቱ ነው) አመለካከት በሀገራችን ለማስፋፋት እንዴት ብንሰራ ይሻላል በሚል መንግሥት ለረጅም ጊዜ ሲመክር ቆይቷል" በማለት የሰጠው አስተያየት ምንም እንኳ የፕሮፓጋንዳ አፈቀላጤዎች ሊያስተባብሉ ቢጥሩም አገዛዙ ይህንን ሃይማኖታዊ አስተምርዎት ለማስፋፋት ምንኛ ሲያሴር እንደነበረ የሚጠቁም ነው።

የእምነት ነፃነት መብት ተግባራዊ በሚሆነበት ወቅት ገደብ የሚበጅለት የሌላን ዜጋ መብት ያለማክበር ወይንም እምነቱን የተሳሳተ አድርጎ በመቁጠር ለመጋፋት የተንቀሳቀሰ እንደሆነ ግልፅ ነው። ይህ ሁናቴ በጣም በሚያሳዝን ደረጃ ወያኔ ሥልጣን ከያዘ በኋላ በክርስትና እምነት ተከታይ ነን በሚሉት ምዕመናን በፅሁፍና በቪዲዮ ተቀርፀው በተለያዩ ድረገፆች አማካኝነት የተነዙትን ምንም አይነት የመከባበር ስሜት የሌለባቸው፤ አንዱ በሌላው ላይ የበላይነት ለማግኘት የተደረጉና ለመስማት የሚቀፉ የጥላቻ ዘመቻዎችን በአግራሞት የምናስታውሳቸው ነው። በክርስትና እምነት በተለይም የኢትዮጵያ ተዋህዶ የክርስትና እምነት ተከታዮችን ከኢትዮጵያዊነትና አንድነት ጋር በማያያዝ የነበሩ የጥላቻ ዘመቻዎችና ግድያዎችም የዚሁ የወያኔ አገዛዝ ፖሊሲ ነፀብራቆች የነበሩ አሁንም ድረስ የቀጠሉ ናቸው።

የሃይማኖት እምነት መከበርና ዋስትና ማግኘት የሚመሰረተው በተለይ ማንኛውም ግለሰብ ፈጣሪዬ ከሚለው ጋር በሃይማኖቱ መሠረት ግንኙነት ለማድረግ ባለው ፍላጎትና ይህም ስኬታማ ይሆን ዘንድ ባለው ችሎታ ላይ ነው። የሃይማኖት ነፃነት የሚረጋገጠው በተቋማቸው ነጻነትና በዚሁ ነፃነት ተመርኩዘው በሚያደርጓቸው እንቅስቃሴዎቻቸው ነው። የፖለቲካ ነፃነት ሲባልም የተፃፈበትን ወረቀት ያህል እንኳ ክብደት የሌለው ሕገ-መንግሥት በሚባለው ሰነድ ላይ መስፈሩ ሳይሆን በገቢር ለሕዝብ በተለይም ለብዙሃኑ የሚጠቅም ሆኖ ሲገኝ ነው። ያለፉቱን አገዛዞች ስንመለከት በርካታ መብቶችን የሚያረጋግጡ አንቀፆች በሰነዶቻቸው ያካተቱ ቢሆኑም በተግባር እንደታየው መብትም ሆነ እኩልነት ተከብረው አልታዩም። ውጤቱም ለውድቀት መዳረጋቸው ነው።

በሀገራችን በአሁኑ ወቅት ይህ መብት በዋናነት በአገዛዙና የሱን ፈለግ በሚከተሉ ቡድኖች ብሔሬ ነው የሚሉትን ማህበረሰብ በነፃ እናወጣለን ሰበብ በግል ቁጥጥር ለማስገባት ካላቸው ፅኑ ፍላጎት በመነጨ፤ የእውነት ቃል ከኔ ሃይማኖት የምትገኝ ከሚል ግብዝነት ላይም በመመርኮዝ ብቻ ሳይሆን በኢትዮጵያዊነት ላይ አስፀያፊ ዘመቻ በማካሄድ በከፍተኛ ደረጃ እየተጣሰ ይገኛል። ተደጋግሞ እንደተገለፀው ባለፉት 22 አመታት የወያኔ አገዛዝ ከዚህም ከዚያም ካሉ የባዕዳን ሕጎች እየለቃቀመ በሕገ አገዛዙ ሽጉጦ የሃይማኖት ነፃነት አረጋግጫለሁ እያለ መጠነ ሰፊ ፕሮፓጋንዳ ቢነዛም በሃይማኖት ተቋማት የውስጥ ጉዳይ እጁን በጥልቀት ማስገባቱ ብቻ ሳይሆን በተቋማቱ ውስጥ ሰግስጎ ባስገባቸው ካድሬ ካሕናቶችና ሃጂዎች/ኢማሞች የምዕመናኑን መብትና የተቋማቸውን ነፃነት በመጋፋት ከፉኛ የመብት ጥሰት እያደረገ ይገኛል። ስለሆነም በነዚህ የሃይማኖት ተቋማት ውስጥ በአገዛዙ አማካኝነት በመሪነት የተቀመጡት ግለሰቦች ለፈጣሪያቸውና ለሕገ ሃይማኖታቸው ሳይሆን ለአገዛዙ ታማኝ አገልጋይ ሆነው በምዕመናኑ ትከሻ ላይ ሳይወዱ በግድ ተቀምጠውባቸው በርካታዎች ለስቃይ ሰለባነት ተዳርገዋል። ሃይማኖታዊ ተልዕኳቸውን ለምዕመናኑ በተገቢው ደረጃ ለማበርከት ባለመቻላቸውም እየቀረበባቸው ያለው ተቃውሞ ግለቱ በየጊዜው እየጨመረ ይገኛል።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ለሁለት ተከፍላ አንዱን በሀገር ቤት ሌላኛውን ደግሞ በውጭ ሀገር ሁለት ፓትሪያርኮችን ለማስተናገድ የተገደደችበት ምክንያት ይኸው የአገዛዙ የጣልቃ-ገብ እጁን በስፋት በማስገባቱ ነው። አቡነ መርቆሪዎስ ከመንበራቸው የተፈናቀሉትና የተባረሩት ዛሬ በስደት በሚገኘውና በወቅቱ የወያኔ ጠ/ሚኒስቴር በነበረው ግለሰብ ፊርማ መሆኑም የሚረሳ አይደለም። የወያኔ አገዛዝ በዚህም ብቻ ባለመርካቱ በተለይ በውጭ ሀገር ያሉ ቤተክርስቲያናት በጎተ የመከፋፈል አባዜም

እንዲናወጡ በካድሬዎቹ አማካኝነት በስፋት እየተንቀሳቀሰ ለመሆኑ በየቦታው የሚታዩትና የሚደመጡት አለመግባባቶች የሚያመላክቱት ነው። ይህ ድርጊት የቤተክርስቲያኒቷን ውስጣዊ ሕግ የሚፃረር፤ በውስጥ ጉዳይ ጣልቃ መግባትና ነፃነቷን መርገጥም ነው።

የወያኔ አገዛዝ "ቅድሚያ ለልማት" በሚልም ሆነ በብሔራዊ "ደህንነት" በማሳበብ በተለይም መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን ለመቆጣጠር ባለው ፅኑ ፍላጎት የተነሳ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት አዋጅ እንዲሁም የፀረ-ሽብርተኝነት ሕግ ተብየውን በ2002 ዓ.ም ካወጀ ወዲህ በኢትዮጵያ ሀሳብን በነፃ የመግለፅ፤ የመሰብሰብና የመደራጀት መብቶችን በከፍተኛ ደረጃ ደፍጥጧል። ለዴሞክራሲያዊ ግንባታ ወሳኝ ሚና ሊጫወቱ የሚችሉት የሲቪል ማህበረሰቦች እንደ ሕይወት እስትንፋስ የሚገለገሉበትን መድረኮቻቸውን በቻለበት ዳግም እንዳይንሰራሩ አፍርሷል፤ ሳይቻለው ሲቀር የራሱ ተለጣፊ አድርጎ ተግባሮቻቸው እንዲተጓጎሉ አድርጎባቸዋል። በአንድ ለአምስት ቀመሩም አባላቱን ለመቆጣጠሪያ ይጠቀምባቸዋል። ይህ የመብት ድፍጠጣ የተጀመረው ሥልጣን ከተቆናጠጠ ከ22 ዓመት በፊት ሳይሆን ከዛ ቀደም ብሎ እንደነበር የእንቅስቃሴ ታሪኩ የሚመሰክርበት ነው። በክርስትና እምነት ተከታዮች ብቻ ሳይሆን ባጠቃላይ አማኚያን በነበረበት ወቅት ያራምድ የነበረውን ፖሊሲ ያልተቀበሉና ለሱ ያላጎነበሱ በርካታ የትግራይ ተወላጆች ላይ የተፈፀመው አሳዛኝና አሰቃቂ ግፍና በደል ከቶም የማይረሳ አሁንም በቀጣይነት እየተካሄደ ያለ ክስተት ነው።

ፖለቲካና ሃይማኖት ሳይደበላለቁ በየመስኮቻቸው ሊሰሩ ይገባል የሚል የፀና እምነት ያለው ኢሕአፓ "ሃይማኖት የግል ነው ሀገር የጋራ ነው" በሚልም በመንግሥትና በሃይማኖት ተቋማት ሊኖር የሚችለውን ግንኙነት አስመልክቶ ከሃይማኖት ተቋማት ዝርዝር የሆነ የፖለቲካ ፕሮግራምና የሰላም ስትራተጂ ሊያቀርቡ እንደማይጠበቅባቸው ይገነዘባል። እንዲያውም በተቃራኒው በዚህ ጎዳና እንዲሰማሩ የሚያደርጓቸውን ማናቸውንም ጥረቶችና ግፊቶችን የኃይማኖት አባቶች ሊቋቋሟቸው የሚገባና በዚህም የሌላውን የሕብረተሰብ ክፍል ሙሉ ድጋፍ ሊጠይቁ የሚገባቸው እንደሆነ ይረዳል። ከተመክሮ እንደሚታወቀው በራሳቸው ዋና አቀናባሪነትና ሥልጣን ያዢነት የፅድቅ ቦታን በላይኛው ዓለም እየሰበኩ በምድር ግን ገሀነምን የመሰለ ኑሮና ሥርዓት መሥርተው የበርካታ ምዕመኖቻቸውን ሕይወት ብቻ ሳይሆን የነሱን እምነት ያልተቀበሉ ዜጎችን ጭምር ለሕልፈት የዳረጉ፤ ለተለያዩ የመንፈስም ሆነ የአካል ጉዳት መድረስ ምክንያት የሆኑ በመሆናቸው ጉዳዩን ሁሌም በጥንቃቄ እንድንመለከትው የሚያስገነዝብ ነው። እምነት ደግሞ ስሜትን ኮርኳሪ ናትና፤ በእምነቱ የሚፀና ሕይወትን ለመስዋዕት ለማቅረብ እምነቱ ለዚህ የሚያስፈልግን የመንፈስ ውስጣዊ ኃይልና ብርታት የሚሰጥ በመሆኑ በንፁህ ልቦና ማየትን የሚጠይቅ ነው። ለዚህም ነው ሃይማኖትና መንግሥት ተለይተው እንዲዋቀሩ ማድረግ መሠረታዊ የሚሆነው። ይህ ደግሞ ፀረ-ሃይማኖት ሆኖ እምነትን ከፖለቲካው መድረክ ማጥፋት ማለት አይደለም። ይልቁንም በሃይማኖቶች መካከል የተዛባ ልዩነትን በማጥፋት እኩልነትን በመካከላቸው ለማስፈን ነው። ሃይማኖትና ፖለቲካ ተለያይተው እንዲዋቀሩ የማድረግ የመርሁ ፅንስ የሚመሰረተውም በዚሁ በግለሰብ መብት ላይ ነው። የሃይማኖት እምነት ተልዕኮን በሚመለከት እንደ ተቋም በሕብረተሰቡ ውስጥ ሊያበረክት የሚችላቸውን አስተዋፅዖ በሚገባ መገንዘቡ በሃይማኖትና በፖለቲክ መካከል ሊኖር የሚችለውን ግንኙነት በጥሩ መሰረት ላይ ለመገንባት የሚረዳ ነው። የመለያየታቸውና የመተባበራቸው ሂደት ከተለያዩ ሀገሮች ተመክሮ ለመረዳት እንደሚቻለውም ወርድና ስፋቱ ከሀገራችን የባህልና የአኗኗር ሁኔታ ጋር በሚጣጣም መልኩ ማደራጀትና መገንባት ወሳኝ መሆኑን መጥቀሱም ከዚህ አንፃር አግባብነት የሚኖረውም በዚሁ የተነሳ ነው።

የፖለቲካ ፕሮግራም የተወሰነ ሁናቴን ብቻ የሚመለከት ሳይሆን ተጨባጭ ውሳኔንና ተግባራትን ሊመሩ የሚችሉበትን ጠቅላላውን መስክ ጭምር ነው። በዴሞክራሲ ሥርዓት ይህ ፖለቲካዊ የሆነ መሠረታዊ አቅጣጫ ሰጪነት ከሀሳብና ከፍላጎት ግንባታ ውይይት የሚመነጭ ነውና የሃይማኖት እምነት ተከታዮችም

በዚህ ውይይት ውስጥ እንደማንኛውም ዜጋ ተካፋይ የመሆንና ሀሳባቸው ተቀባይነት እንዲያገኝ ለመንቀሳቀስ ያላቸው መብት የተጠበቀ ይሆናል። በዚህ ሁኔታ ነው የሃይማኖት አስተምህሮትና የፖለቲካው አርቆ አስተዋይነት ሊገናኙ የሚችሉት።

በሀገራችን የሚገኙት እምነቶች በተለይም በርካታ ተከታዮች ያሏቸው የክርስትናና የእስልምና ሃይማኖች መካከል በአርዓያነት ሊታይ የሚችል ድንቅ የሆነ የመቻቻል፤ የመከባበር፤ የመተጋገዝ ባሕልን ያሳዩ ለመሆናቸው እኛ ይህንን ታሪካቸውን የወረስነው የአሁኑ ትውልድ አባላት ብቻ ሳንሆን የዓለም አቀፍ ሰላም ወዳድ ኃይል ሁሉ የሚመሰክሩልን ነው።ዕውነታው ይህ ሆኖ ሳለ ቀደም ብሎ እንደተጠቆመው ይህንን የመቻቻል እሴት መሠረቱን ሊያጠፉ የሚችል፤ በእምነቱ ተከታዮች መካከል ወደ የማያቋርጥ ብጥብጥ ሂደት ሊወስድ የሚችል እንቅስቃሴ ማስተዋል ከጀመርን በርካታ ዓመታት ያስቆጠረ ቢሆንም ባለፉት ሁለት ዓመታት ግን በእጅጉኑ ተባብሶ ይገኛል። የሩቁን ትተን በ1999 ዓ.ም መግቢያ ለምሳሌ በኦሮሚያ በጅማና በኢሉባቡር ነዋሪ የሆኑ ዜጎች በእስልምናና በክርስትና አማንያን መካከል በሺዎች ለሚቆጠሩ አመታት የኖረውን የመከባበርና የመቻቻል ድንበር የጣሰ ዘግናኝ ግጭት ተከስቶ ለበርካታ ዜጎች ሕይወት መጥፋትና ሰላም ማጣት፤ ለንብረት መውድም ምክንያት ሆኗል። በባሌ፣ በአርሲና በሀረር፤ በወሎም ተመሳሳይ አክራሪነትና ጽንፈኝነትን መነሻ ያደረጉ እንዲሁ ለሕሊና የሚቀፉ ድርጊቶች ተፈጽመዋል። ወያኔ ሕዝብን ለማጣላት ራሱም በስውር የፈጸማቸው ወንጀሎችና ጥቃቶች ጥቂቶች አይደሉም ።

የወያኔ አገዛዝ ስለ ፍትህ፤ መልካም አስተዳደርም ሆነ ስለ ዴሞክራሲ የሚያነሆልሉ አረፍተ ነገሮችንና አንቀፆችን እየደረደረ ሕዝብን ለማታለል እንደሞከረው ሁሉ ሃይማኖትንም በሚመለከት "መንግሥትና ሃይማኖት የተለያዩ ናቸው፤ መንግስታዊ ሃይማኖት አይኖርም፤ መንግሥት በሃይማኖት ጉዳይ ጣልቃ አይገባም፤ ሃይማኖትም ከፖለቲካ ይርቃል" የተባለውን ጥሶ ጣልቃ በመግባት፤ ሁሉን ነገር በራሴ ሙሉ ቁጥጥር ሥር ካላደረግሁ በሥልጣኔ ለመቆየት አልችልም የሚል አባዜ የተጠናወተው በመሆኑ ይህንን በሙሉ ገፅታው እንኳ ያልተገለፀ፤ የሕግ አንቀጽ በግልፅም ሆነ በስውር በመጣስ የኃይማኖቱን ተከታዮች እርስ በርስ የሚያጋጭ ተግባር እየፈፀመ ይገኛል። በተወሰነ ደረጃም አልተሳካለትም ለማለት አያስደፍርም።

የወያኔ በሽታ ኢትዮጵያዊ ችግሮቻችንን በኢትዮጵያዊያን ዐይን ለማየትና በፍላጎታችን መፍትሄ ለመስጠት ከመጀመሪያውኑ የተመሰረተበት ራዕዩ የሚፈቅድለት አለመሆኑ ነው። በአፄ ኃይለ ሥላሴ የአገዛዝ ዘመን በወረቀት የሰፈረ የእኩልነት መብት የነበረ ቢሆንም በተግባር ባለመረጋገጡ ሕዝብ በሥርዓቱ ላይ አምፆ ሊስወግደው ችሏል። በዚያን ውቅት የሃይማኖት እኩልነትና የሙብት መረጋገጥ አለመኖሩን በመቃወም የእስልምና እምነት ተከታይ የሆኑ ዜጎቻችን የተቃውሞ ሰልፍ ባደረጉበት ወቅት የክርስትና እምነት ተከታይ ዜጎቻችን አብረው ከጎናቸው በመቆም ለሥርዓቱ መውደቅ የበኩላቸውን አስተዋፅዖ ማበርከታቸው፤ በታሪክ ማህደራችን በሕዝባችን አጥንትና በደም ቀለማቸው የተፃፈ ምንጊዜም የማይረሳ አኩሪ ቅርሳችን ነው። ይህ ክስተት በአሁኑ ጊዜ የማይደገምበትና ሌላ የጀግንነት ታሪክ የማይፃፍበት ምንም ምክንያት አይኖረም። የሚያግደውም ኃይል ሊኖር አይችልም።

ስለሆነም ኢሕአፓ የእያንዳንዱ ዜጋ በተናጠልም ሆነ በወል ተቀናብሮ፤ ዜጎች የርዕዮትና የእምነት አመለካከታቸው እንዲከበርና ሕይወታቸውንም በነፃ ለመምራት ሁኔታው እንዲመቻችላቸው ይታገላል። ይህ በንዲህ እንዳለ ኢትዮጵያ ሀገራችን የተለያዩ ሃይማኖቶች የሚመለኩባትና መድበላዊ ጠባይ ያለው ሕብረተሰብ ያላት በመሆኗ የሁሉም ሃይማኖቶች እኩልነት ያለገደብ ማረጋገጥና ለሰላም መስፈን፤ ፖለቲካና ሃይማኖት በሚገባ ተለይተው የተግባር መድረኮቻቸውም በግልፅ ተወስኖ እንዲቀመጥ ትግሉን ይቀጥላል። የኦርቶዶክስ ተዋህዶና ሌሎች የክርስትና እንዲሁም የእስልምና እምነት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የመንግሥት እምነት እንዲሆኑ የሚደረጉ ጥረቶችን አጥብቆ ይቃወማል። ስለሆነም መንግሥት በሃይማኖት ጥልቃ አይገባም፤ ሃይማኖት የመንግሥትን መንግሥት የሃይማኖትን ሚና መጫወት በሕግ

የተከለከለ ነው እየተባለ ግን የሥርዓቱ ጥገኛ ለማድረግ የሚደረጉ ጥረቶችንም ሁሉ እንዲሁ አጥብቆ ይቃወማል። የሃይማኖት እኩልነትንና የሙብት መከበርን ተንተርሶ የሚደረጉ ዴሞክራሲያዊ ትግሎችን በፅንፈኝነትና አክራሪነት መስመር እንዲጓዙ የሚደረጉ ጥረቶችም ከየትኛውም አቅጣጫ ይምጡ ሀገራችንና ሕዝባችንን አስከፊ ወደሆነ መቀመቅ ውስጥ የሚከታቸው በመሆኑ አጥብቆ መታገልን ያሻል። ምንም እንኳ የፖለቲካ ድርጅቶች በዚህ በኩል ከፍተኛ አርቆ አስተዋይነት የተሞላበት አመራርና የትግል አቅጣጫ ሰጪነት እንዲሁም የመፍትሄ ጠቋሚነት መስጠት የሚጠበቅባቸው ቢሆንም ከነሱ ብቻ የሚመጣውን መጠበቅ ፈፅሞ ትክክል አይሆንም። ጥያቄው ሁሉንም ዜጋ የሚመለከት በመሆኑ ማንኛውም ዜጋ በሚገኝበት ቦታ የየበኩሉን አስተዋፅኦ ሊያበረክት እንዲችል መንቀሳቀስ የግዴታ ነው ሲል ኢሕአፓ ያምናል። በዚህም ይንቀሳቀሳል።

ማንኛውም እምነት በቅድሚያና በዋናነት የሚመለከተው ግለሰብን ነውና መቀበልም ሆነ ያለመቀበል ሁናቴ የሚወሰነው በግለሰብ ብቻ መሆኑ ሊሰመርበት የሚገባ ጉዳይ ነው። ለዚህም ነው እንኳን የተለያዩ እምነቶች በሚንፀባረቁባት እንደኛ በመሰለች ሀገር ቀርቶ አንድ ቋንቋና እምነት ባለበት እንኳ መንግሥትና ሃይማኖት ተለያይተው መኖር ይገባቸዋል ተብሎ አጽንዖት በተሞላበት አኳኋን እየተገለጸ የሚገኘው። ይህ ማለት ግን ለሕዝብ የጋራ ጥቅምና ደህንነት ሲባል በተወሰኑ ጥያቄዎች ሁለቱ ተቋማት አይተባበሩም ማለት አይደለም። እንዲያውም በሚሰማሩባቸው መስኮች ለጋራ ጥቅም መተባበር የግድ ይላቸዋል።

ኢሕአፓ የኦርቶዶክስና የእስልምና እምነቶች በኢትዮጵያ በሕብረተሰባችን ውስጥ በባህልም ሆነ በወጋችን ሥር መሠረት የጣሉ መሆናቸውን ይገነዘባል። ስለሆነም እነዚህ እምነቶች በሕዝባችን ውስጥ የጣሉትና ያሰፈሩትን ተፅዕኖ በግልፅ የሚያየው ነው። ከዚህ በመነሳት ግን ማንኛውም የእምነት ተቋም በሕብረተሰባችን ውስጥ ከተግባር ላይ እየዋሉ ባሉት እሴቶች ብቸኛ የመተርጎም የበላይነት አላቸው ማለት አይደለም። ሁሉም እሴቶች በሕብረተሰቡ አባላት በሞላ ተቀባይነት ለማግኘትም ሆነ ላለማግኘት በቀን ተቀን ተግባራት በመዳሰስ ሊፈተሹና ሊጠኑ ግድ ይላል። በተመሳሳይ ሁኔታም ፖለቲካው ስለ እሴቶች ብቸኛ የመተርጎም ሥልጣንም ሆነ ስለ እምነት ይዘት አቅጣጫ ሰጪ ሊሆን አይገባም። ኢሕአፓን ከወያኔ የሚለይበት አንዱ ነጥብም ይኸው ነው።

የወያኔ አገዛዝ በኢትዮጵያ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ውስጥ እንዳደረገው ሁሉ በእስልምና ጉዳዮች ምክር ቤት ውስጥም ያደረገውንና አሁንም ድረስ እያደረገ ያለውን ጣልቃ ገብነት በመቃወም፤ ይህንን በአደባባይ በሰላማዊ ተቃውሞ ለመግለፅ የወጡ የእስልምና እምነት ተከታዮችን ለመበተን በተለያዩ ቀናት የፌደራል ፖሊስ ከድብደባ አንስቶ ተሳታፊዎቹን ለማሸማቀቅ በታቀደ መልኩ በመሳሪያ የታጀበ ኃይልን ተጠቅሟል። አዲስ አበባ ወደሚገኘው የአወሊያ መስጊድ በኃይል በመግባት ፖሊሶች መስኮቶችን የሰባበሩ ሲሆን በመስጊዱ ውስጥ አስለቃሽ ጭስ በመተኮስ ምዕመናኑን አሰቃይተዋል። በመስጊዱ ለተቃውሞ ተቀምጠው የነበሩ ሰዎችን ኃይል በመጠቀም እንዲበተኑ አድርጓል። በተለያዩ ወቅቶች በርካታ የእስልምና እምነት ተከታይ ዜጎቻችን ታፍሰው ዘብጢያ እንዲወርዱ ሲደረጉ 17 የመፍትሄ አፈላላጊ ኮሚቴ አባላትና ከፍተኛ የእንቅስቃሴአቸው መሪዎች በቁጥጥር ሥር እንዲውሉ ተደርገው በፀረ-ሽብርተኝነት "ሕጉ" ክስ ተመስርቶባቸው የአገዛዙን የፍርደ ገምድል ውሳኔ በመጠባበቅ ላይ ይገኛሉ።

ከአንድ አመት ከስምንት ወራት ጀምሮ የእስልምና እምነት ተከታይ የሆኑ ዜጎቻችን ለዴሞክራሲና ለእኩልነት ሙብት መከበር፡ ለፍትህና ለመልካም አስተዳደር መመስረት እየታገሉ ይገኛሉ። የወያኔ አገዛዝ ሕዝበ ሙስሊሙን ማዋከቡን፤ መበደሉንና በሃይማኖታዊ ጉዳያቸው ጣልቃ ገብነቱን እንዲያቆምና በሌሎች መሰል የሙብት መከበር ዙሪያ ጥያቄዎችን በማቅረብ በተለያዩ የሀገሪቱ ከተሞች የሚኖሩ የእስልምና እምነት ተከታይ የሆኑ ዜጎቻችን እያደረጉ ያሉት ትግል ከጊዜ ወደ ጊዜ ግለቱ እየጨመረ መሄዱ በገሃድ የሚታይ ነው - ሊደገፍና ሊደነቅ የሚገባው ትግል። ይህ አልገዛም ባይነትና የሲቪል ወኔን የተላበሰ

ትግላቸው የተሳሳተና ልዩ ትርጉም እየተሰጠው ቢገኝም ሳይሸማቀቁ ይበልጡኑ ትግላቸውን በቆራጥነት በመቀጠል እያፋፋሙት ይገኛሉ።

ምንም እንኳ በጥቂት ሳምንታት ውስጥ የተፈረሙ በሚሊዮን የሚቆጠሩ የድጋፍ ፊርማ ያገኙትን በሙስሊሙ ማህበረሰብ የቀረቡትን ጥያቄዎችን የአገዛዙ የፕሮፓጋንዳ አፈቀላጤዎች ዋጋ ለማሳጣት የማስመሰያ ጥያቄዎች እያሉ ቢፈሩጁቸውም ተገቢነታቸውንም ሆነ መሰረታዊነታቸውን ስለማይቀይረው ለግልፅነት ይረዳ ዘንድ ጥያቄዎቹን እዚህ ማንሳቱ አግባብነት አለው። በመሆኑም በሙስሊሙ ማህበረሰብ የቀረቡት ጥያቄዎች፡-

1. የሙስሊሙን መሪዎች (መጅሊስ በኢትዮጵያ የእስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት) እኛው ራሳችን ሙስሊሞችን በሚወክልና በሚያሳትፍ መንገድ በመስጊዳችን ያለ ወያኔ ካድሬ ታዛቢነት፤ ያለ አገዛዙ እጩ ተወዳዳሪ አቅራቢነት እንምረጥ፤
2. ሃይማኖታችንን ለማመንና ለማራመድም እኛው በመስጊድ ውስጥ በመረጥናቸው የመጅሊሱ አባላት መሪዎቻችን ብቻ እንመራ፤
3. አገዛዙና ወያኔዎች አህባሽ በሚባል የሙስሊም ሃይማኖት ያሰለጠናቸው ካድሬዎች የአገዛዙ ባለሥልጣን የሆኑ ሙስሊሞችን ለመምራትና በሃሰት ለማስመሰል ለመስበክ ካልሆነ በስተቀር ሰፊውን የሙስሊሙን ማህበረሰብ አይወክሉም፤
4. አህባሽ የተባለው እምነት እንደማንኛውም እምነት ራሱን ችሎ የመንቀሳቀስ መብት ይኖረዋል እንጂ በሙስሊሙ መስጊዶችና መዋቅር ውስጥ በግድ እንዲጫን ሊደረግ አይገባውም፤
5. አወሊያ የሕዝብ ንብረት እንደመሆኑ መጠን እራሱን በአግባቡ ማስተዳደር ለማይችለው መጅሊስ መሰጠት የሌለበት ሲሆን ሕዝብ በሚመርጣቸው የቦርድ አባላት ይተዳደር፤
6. በአጠቃላይ ለሙስሊሙ ትክክለኛ ሃይማኖት መራጭ ምዕመናኑ እንጂ የወያኔ ካድሬዎች መሆን የለባቸውም። በሙስሊሙ ሃይማኖት አገዛዙ ጣልቃ አይግባብን

የሚሉ ናቸው።

እነዚህ የሙስሊሙ ማህበረሰብ ጥያቄዎች ከ2003 ዓ.ም. መጨረሻ ጀምሮ እስከ ዛሬ 2006 በሚሊዮን በሚቆጠሩ የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች ተደግፈውና ተጠናክረው እየቀጠሉባቸው ብቻ ሳይሆን የመብትና የዴሞክራሲ ጥያቄዎች መሆናቸው ግልጽ ሁኖም እያለ የወያኔ አገዛዝ ግን ጥያቄያቸው የእምነት ጥያቄ ሳይሆን እምነትን ከለላ ያደረገ፤ የከሰሩ ፖለቲከኞች የአክራሪነት አዝማሚያ ነው በማለት በከፍተኛ ደረጃ እየወነጀለ ለማጥላላት እየጣረ ይገኛል። ሁናቴውን በሚገባ ባለመረዳት የወያኔ አገዛዝ የሚያስተጋባውን ፕሮፓጋንዳ ተቀብለው ያመኑ ዜጎችን ስናስብ ደግሞ በከፊል አልተሳካለትም ብሎ ለመናገር የሚከብድ ነው።

የወያኔ አገዛዝ በሙስሊሙ ማህበረሰብ ለቀረበለት ጥያቄ እየሰጠ ያለው መፍትሄ የመብት መከበር ሳይሆን መከፋፈልና ማስፈራራት፤ ተደጋጋሚ በእውነት ላይ ያልተመሰረተ ፊልም በማዘጋጀትና በሞኖፖል በያዘው የዜና ተቋም ማሰራጨት፤ በተለያዩ ጥቅማ ጥቅሞች በመደለል ማኮላሸት፤ ሲጠጥር ደግሞ የአፈና ተግባሩን አጠናክሮ መግፋት ነበር፤ አሁንም ነው። ይህንን የተገነዘበው የሙስሊሙ ሕብረተሰብ ግን እየተሰጠው ያለው መልስ የተሳሳተና የማያዋጣ፣ ተቀባይነትም የሌለውና አደገኛ መሆኑንም በመረዳት ቢጫ ካርዱን በማውለብለብ የማስጠንቀቂያ ደወሉን በማያሻማ ሁኔታ በአደባባይ አሰምቷል፤ ድምፁን በመላው ሀገሪቷ

አስተጋብቷል። ትዕግሥቱ ወሰን የለሽ አለመሆኑንም በሚገባ ይፋ አድርጓል። በቅርቡም ቢሆን የእስልምና እምነት ተከታይ ዜጎቻችን፣ ለአደጋ ላለመጋለጥ ሆኖም ግን ብስለታቸውን የሚያሳየውን የዝምታ ተቃውሟቸውን በአዲስ አበባ ማድረጋቸው የሚያረጋግጠው ይህንኑ ነው። ያቀረቡት የሙብት ጥያቄ አግባብ በሆነ መልኩ መፍትሄ ካላገኘም ትግላቸው ቀጣይ እንደሚሆንም በእንቅስቃሴ ተግባራቸው ግልፅ የሆነ መልዕክት አስተላልፈዋል። በሚገባ ሊደመጥ የሚገባው ደወል ነው ያቃጨሉት።

ዛሬ በግልፅ እንደሚታየው የሙብት ጥሰቶችና በደሎች እየተደረገ ያለው በእስልምና እምነት ተከታዮች ብቻ ሳይሆን በተለያዩ የክርስትና እምነት ተከታዮችም፣ በሠራተኛው፣ በአስተማሪና ተማሪው፣ በሠራተኛና ገበሬው፣ በአምራቹና በሸማቹ፣ በሴቱና በወንዱ፣ ባጠቃላይ በሁሉም የሕብረተሰብ ክፍል ላይ ነው። ለዚህም ነው የሙስሊሙ ሕብረተሰብ የነዚህ ሁሉ አካል እንደመሆኑ መጠን ትግላቸው እንዳለፈው የየካቲቱ 66 እንቅስቃሴ ሀገራዊ አንደምታና ኢትዮጵያዊነት የተላበሰ ነው። ለዚህም ነው ማንኛውም ዜጋና የሕብረተሰብ ክፍል ይህንን የሙስሊሙን ትግል ራቅ ብሎ በጥርጣሬ መመለከት ሳይሆን ከልብ ሊደግፈውና ትግሉን የራሱ ትግል አድርጎ ሊያግዛቸው፤ በጋራ ተባብሮና አምርሮ የጋራ ችግራቸው መሠረት የሆነውን የወያኔን አገዛዝ መታገልና ማቸነፍ ኃላፊነቱና ግዴታው የሚሆነው። ባለፉት ጊዜያት በተከታታይ የተደረጉት የተቃውሞ እንቅስቃሴዎች ያስተላለፉት መልዕክትና ያሰሙት ቃጭል የእንደ.ጋገፍ ጥሪ ደወል ነበር። በመሆኑም ማንኛውም ዜጋ በግላጭ ወጥቶ በትግሉ በመሳተፍ ላለፉት 22 ዓመታት የተሸከመውን የጭቆናና የበደል ቀምበር ከትከሻው አሽቀንጥሮ ለመጣል በመነሳት ሀገር ወዳድነቱንና ለሕዝብ ቀናዒነቱን በተግባር ማሳየት ይጠበቅበታል።

ኢሕአፓ የመመስረቱ ዋና መነሾ አንዱ ነጥብ የዴሞክራሲና ሰብዓዊ ሙብቶች አለመከበር እንደመሆኑ መጠን፤ ለነዚህ እሴቶች መከበር ሲታገል ከቆየውና አሁንም እየታገለ ከሚገኘው የክርስቲያንና የሙስሊሙ ማህበረሰብ ባጠቃላይም ከታጋዩ ሕዝባችን ጎን መቆምና በግምባር ቀደምትነት መሰለፍ ግዴታው ነውና አሁንም እንደቀድሞው ከጎናቸው በመቆም በፅናት ይታገላል። ደጋግሞ እንደገለፀውም የዜጎቻችን ሙብት ያለምንም መሸራረፍ ሊከበር የሚችለው በጋራ የሁሉንም ዜጋ ሙብት የሚያስከበር፣ ነፃነትን የተላበሰና በሱ መርህ ላይ የሚመሠረት ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ተገንብቶ ሕዝብ የሥልጣን ባለቤትነቱን፣ የሥልጣን ምንጭነቱን በገቢር ሲያረጋገጥ ነው።

የእባብ እንቁላል ቀፍቅፎ የሰላም እርግብን ማግኘት እንደማይቻል ሁሉ፤ የአፈና ኃይልን አቅፎ ነፃነትን መጎናፀፍም የሚታሰብ አይሆንም። ድል ካልተወደቁላት፣ ደምን ካላፈሰሱላትና አጥንትንም ካልከሰከሱላት ደግሞ በምኞት ብቻ ከእጅ አትገባም። የወያኔ አገዛዝ የመውደቂያው ጊዜ እየተፋጠነ መሆኑ የሚታይ ነው። ወሳኝ ምቱን በጋራ የሕዝብ ትግል ካላገኘ ደግሞ እየተንገዳገደም ቢሆን በሥልጣኑ መቆየቱና ሕዝብን መበደሉ ቀጣይነት ይኖረዋል። ለኛ ዴሞክራሲ ሂደትና ዜጎች እርስ በርስ ግንኙነታቸውን የመምራት፣ በፖለቲካ ውሳኔ ሂደት ተካፋይ መሆን፤ ለሕብረተሰብ ኃላፊነት በተለያዩ ትከሻዎች እንዲከፋፈል ማድረግ በመሆኑ ለዚህ በቅድሚያ እንቅፋት የሆነ ኃይልን ማስወገድና ሂደቱ እንዲጠናከር ያላሰለሰ ጥረትን ይጠይቃል። የወያኔን አገዛዝ እንዳይቀጥል ማድረጉ ጊዜው ከምንጊዜውም በበለጠ በአሁኑ ወቅቱ እየጠየቀ ነውና ይህንን አጋጣሚ ብልህነትና አርቆ አስተዋይነት በተሞላበት ሁኔታ ተግባራዊ እናድርገው ሲል ኢሕአፓ የትግል ጥሪውን ያቀርባል።

የፖለቲካ ነፃነትና የዜጎች እኩልነት ይከበር!!

ኃይማኖትን ለግል መሰሪ ተንኮል መጠቀሚያ ማድረግ ወንጀል ነው!!

በተባበረ ትግል የወያኔ አገዛዝ ይወገዳል!